# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net

sh1@ttomar.net

---

ገ_ዐዓ_201701_ዐማርኛ

**የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የ 2017 ፡ ዓ.ም. ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦**

## « የመሸጋገሪያ ፡ ዘመን ፡ ይኹንልን ! »

---

ለንደን ፤ መስከረም ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፤ እግዚአብሔር ፤ እንኳን ፡ ለ 2017 ፡ ዓ.ም. ፡ በደኅና ፡ አደረሰኽ ፡ እያለ ፡ ውጥን ፡ አካልኽ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ( ኢ.ሀ.ሥ.አ. ) ፡ ላዲሱ ፡ ዓመት ፡ የድል ፣ የአንድነት ፣ የነጻነት ፡ እና ፡ የሰላም ፡ ምኞቱን ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ ያቀርብልኻል ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

በ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢትዮጵያ ፡ የደረሰውን ፡ የመንግሥታዊ ፡ ሥርዐት ፡ ለውጥ ፡ 51ኛ ፡ ዓመት ፡ ዘንድሮ ፡ ስናስታውስ ፤ እስከዚህች ፡ ዕለት ፡ ድረስ ፡ ውድ ፡ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ መዳፍ ፡ ሥር ፡ መማቀቋንም ፡ በሐዘን ፡ እናስባለን ። በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ዘመን ፤ የኢትዮጵያ ፡ ስያሳዊ ፡ ኹኔታ ፡ በደም ፡ ዐበላ ፡ ደፍርሶ ፡ መኖሩን ፡ " በፍጹም ፡ አልቀበልም ! በቃኝ ! " ብለኽ ፤ አንተ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፡ ዐምሐራ ፤ ከጥቂት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በፋኖነት ፡ ተደራጅተኽ ፡ በመዋጋትኽ ፡ እና ፡ ተፈላጊውን ፡ መሥዋዕትነት ፡ በመክፈልኽ ፤ እንሆ ፤ የመከራኽ ፡ እና ፡ የደም ፡ መፋሰስኽ ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ የኾነውን ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ን ፡ እና ፡ ሕገ ፡ ውንብድናውን ፡ ከእነግብር ፡ ዐበሮቹ ፡ ገርስሰኽ ፡ ልትጥላቸው ፡ ተቃርበኻል ።

የትግልኽ ፡ መነሻም ፡ መድረሻም ፡ የሀገራዊ ፡ እግዚእናኽ ፡ መከበር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ከግራም ፡ ከቀኝም ፡ መንገድ ፡ ሊያስቱኽ ፡ የሚጐነታትሉኽን ፡ በትዕግሥት ፡ እና ፡ በዘዴ ፤ ሲያስፈልግም ፡ በኀይል ፡ እየመከትክ ፡ ዐልፈኽ ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥትኽን ፡ በመመሥረት ፡ እና ፡ በዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ዘላቂውን ፡ መንግሥትኽን ፡ በመከወን ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ አስከብረኽ ፡ ዐላማኽን ፡ ትፈጽመዋለኽ ፡ ሲል ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ሙሉ ፡ እምነቱን ፡ ይገልጽልኻል ።

www.slttunhzb.net

sh1@ttomar.net

በትግሉ ፡ አመራር ፡ ረገድ ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ያቀረበልኽም ፦

"ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡

ሀገራዊ ፡ ቅያስ ። "

( www.slttunhzb.net )

በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እና ፡ በፋኖ ፡ መሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ሰፊ ፡ ተቀባይነትን ፡ በማግኘቱ ፥ ኹሉንም ፡ ከልብ ፡ እያመሰገነ ፥ ኀይላችንን ፡ በማዋሐድ ፡ 2017 ፡ ዓ.ም.ን ፡ የድል ፡ ዓመት ፡ ልናደርገው ፡ እንደምንችል ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ሙሉ ፡ እምነቱን ፡ በድጋሚ ፡ ይገልጽልኻል ፨

ትሑት ፡ አገልጋይኽ ፦

**ኢ.ሀ.ሥ.አ.**

